ለቅንጅት 1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የአብይ ኮሚቴ ሪፖርት

ክቡር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል
የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ፕሬዚዳንት
የተከበራችሁ የቅንጅት የላዕላይ ምክር ቤት አባላት
የተከበራችሁ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት
እንዲሁም ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች
ክቡራትና ክቡራን

በቅድሚያ ሁላችንም እጅግ ውስብስብ የሆኑ በርካታ ችግሮችን አልፈን እንዲህ ለመገናኘት በመብቃታችን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡

እናንተም ብሩህ ተስፋ ሰንቀን የጀመርነውን ትግል ለመቀጠል ጋሬጣውን ተሻግራችሁ፣ ችግርና መከራውን ተቋቁማችሁ ዓላማችንን ከግብ ለማድረስ በሚተልመው ጉባኤ ለመሳተፍ በመምጣታችሁ እጅግ አመሰግናለሁ፡፡

ሰላማዊ ትግሉን ከዳር ለማድረስ በየአቅጣጫው የወደቁትን በኢትዮጵያ ምድር ፍትህ እንዲነግሥ በተለያየ የትግል ምዕራፍ ሕይወታቸውን ያጡትን ወገኖቻችን በአንድ ደቂቃ ጸሎት ብድግ ብለን እንድናስባቸው እጠይቃለሁ፡፡

በመስከረም 14/1998 ዓ.ም አራት ፓርቲዎች በመዋሀድ የቅንጅት ፓርቲ መከናወኑ በሁሉም ጉባኤተኛ ዘንድ በግልፅ የሚታወቅ ነው፡፡ በፓርቲያችን ጠቅላላ ጉባኤ ማድረግ ያለበት በደንባችን መሠረት በየሁለት ዓመት ሲሆን አሁን ግን ባጋጠመን የተለያዩ ችግሮች ምክንያት በተሰጠው የጊዜ ገደብ መሠረት አልተካሄደም፡፡ ፓርቲው የደረሱበትን ውስብስብና ጥልፍልፍ ችግሮች በፅኑ የትግል መንፈስ በመወጣት እነሆ የፓርቲውን የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባኤ ጠርቷል፡፡ ይህን ጠቅላላ ጉባኤ ለማዘጋጀት የጠቅላላ ጉባኤ አዘጋጅ ዐቢይ ኰሚቴ ተቋቁሞ ባለፉት ወራት ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

ዐቢይ ኰሚቴው በሥሩ የመስተንግዶ፣ የሕዝብ ግንኙነት፣ የፋይናንስና አስተዳደር እና የጥበቃና ደኅንነት ኰሚቴዎችን አዋቅሯል፡፡ እነዚህ ኰሚቴዎችም እንደዚሁ ሌሎች ንዑሳን ኰሚቴዎችን በማቋቋም በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ የፓርቲው አመራርና ሌሎች አባላት በተቋቋሙት ኰሚቴዎች አማካኝነት አስፈላጊውን

መሰናዶ አድርገው ይኸው ለዛሬይቱ ዕለት ደርሰናል፡፡ ፓርቲው ካሉበት ችግሮች ለዘለቄታው ተላቆ የትግሉን ፈር ቀዳጅ የሆነ ምግባሮችን ተግባራዊ የሚያደርግበትን እቅድ ከጠቅላላ ጉባኤ አባላት ለመዘርጋት እነሆ ታሪካዊ ዕለቷ ዛሬ ነች፡፡

በዚህ ጠቅላላ ጉባኤ ከተለያዩ የፓርቲው አካላት ሪፖርት የሚቀርብ ሲሆን በእኔ በኩል ያለፉት ወራቶች እንቅስቃሴዎች ውስጥ በፓርቲያችን ታሪክ ተጠቃሽ የሆነውን ጉዳይ አቀርባለሁ፡፡

በፓርቲያችን ውስጥ የፓርቲውን ፕሮግራምና ደንቦችን የማፍረስ ተልዕኮአቸውን በአገር ውስጥም ሆነ በባህር ማዶ ያለመታከት ሲያካሂዱ የነበሩ ግለሰቦች በመካከላችን እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ ይህንን እኩይ የሆነ ተግባራቸውን በአጭሩ ማክሸፍ ተገቢ መሆኑን የተረዱት ክቡር ፕሬዚዳንታችንም ፓርቲው ለከፋ አደጋ ከመዳረጉ በፊት በግለሰቦቹ ላይ ጊዜያዊ እገዳ የማድረግ ወቅታዊ እርምጃ ወስደው ለማዕከላዊ ምክር ቤት ውሳኔ እንዲቀርብ መመሪያ አስተላለፉ የፕሬዚዳንቱን መመሪያም ተግባራዊ ለማድረግ የላዕላይ ምክር ቤት አባላት በጉደዩ ላይ መክረውና ወስነው በአገር ውስጥ የሚገኙ አባላት በአሉት የመገናኛ መንገዶች ተጠራርተው በመገናኘት በተሰጠው የፕሬዚዳንቱ ጊዜያዊ የእግድ ጉዳይ ላይ ውሳኔ እንዲሰጡ ታስቦ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የላዕላይ ምክር ቤቱ አባላት ኮረም ሞልተው ባለመገኘታቸው በወቅቱ ተሰባስበው ውሳኔ ሊያስተላልፉ አልቻሉም፡፡ በመሆኑም በጽ/ቤቱ ተዘጋጅቶ የበረው አጀንዳና የውሳኔ ሃሳብ በሥራ ላይ ሊውል አልቻለም፡፡

የታገዱትን ግለሰቦችና ተከታዮቻቸውን ለማስታረቅ ይቻል ዘንድ በራሳቸው አነሳሽነት የሽምግልና ተግባር ለማከናወን ከተነሳሱ የፓርቲው አባላትና ደጋፊዎች ጋር የፓርቲያችን ጽ/ቤት በመነጋገር ወደ እርቅ ለመምጣት ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል፡፡

ለሽማግሌዎች የማስታረቅ ጥረት ተግባራዊነት የክቡር ፕሬዚዳንታችን በመሀላችን መገኘት ከምንም በላይ ጠቃሚና አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ በአገር ውስጥ የነበርነው የፓርቲው ከፍተኛ አመራር አባላት የዕርቁን ሂደት በመከታተል የፕሬዚዳንታችንን መምጣት ስንጠባበቅ ቆየን፡፡

የፓርቲው ፕሬዚዳንት ክቡር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ወደ አገር ቤት እንደተመለሱ እርቁ ይከናወናል ብለን ቅድመ ዝግጅት እያደረግን ባለንበት ወቅት ከወዲያኛው ወገን ሆነው ለዕርቁ ዝግጁ ነን ያሉት ኃይሎች የታገዱትን ግለሰቦች በማቧደን አዲስ ፓርቲ ለማቋቋም የ1500 ሰዎችን ፊርማ በማሰባሰብ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ የሚል ስም ለምርጫ ቦርድ አቅርበው ፈቃድ እንዲሰጣቸውም 14 የላዕላይ ምክር ቤትና ሌሎች አባላትን አስፈርመው የመመስረቻ ጉባኤ ሰኔ 11/2000 ዓ.ም ፈጽመዋል፡፡

በዚህም ምክንያት የነዚህን የራሳቸውን ፓርቲ ካቋቋሙ ሰዎች ጋር ፕሬዚዳንታችን በመሀከላችን ቢገኙም የሽምግልናውን ሂደት ለመተግበር ጊዜው አልፏል፡፡ በመሆኑም ይህ ጠቅላላ ጉባኤ በእነዚህ ሰዎች የተወሰዱትን እርምጃዎች በጥልቀትና በርጋታ በማሰብ በዚህ ጉዳይ ላይ ለታሪክ ያህል ውሳኔ እንዲሰጥ ይጠበቃል፡፡

## ለጠቅላላ ጉባኤው የሚቀርቡ ሪፖርቶች

ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የውህደት ሥነሥርዓት አከናውኖ ጥቂትም ጊዜ ሳይቆይ በምርጫ 97 ምክንያት በተፈጠረው ውዝግብ ከፍተኛ የሆኑ አመራሮቹ እና በየትኛውም ደረጃ ላይ ያሉት አባላቶቹ ላይ በደረሰው እንግልት አማካኝነት ፓርቲው በሚፈልገው መጠን ሊንቀሳቀስ አልቻለም፡፡

የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮችና ሌሎችም የፓርቲው አባላት ከእስር ቤት ከተፈቱ በኋላ ከዚሁ ከፓርቲያችን የወጡ አንጃዎች ዛሬ ከፓርቲያችን ተለይተው መውጣታቸውን በመደበቅ በሚፈጥሩት ሕዝብ የማደናገርና የመከፋፈል ሙከራ ትግሉን በተገቢው መንገድ ለማስኬድ የምንፈልገውን ያህል መጓዝ ለጊዜው አስቸጋሪ ነበር፡፡ ነገር ግን በአዲስ አበባና ከአዲስ አበባ ውጭ በሚገኙ ጠንካራ አባላቱ ፓርቲው ከተጠነሰሰለት ፍፁም ሕልውናውን የማጥፋት ጥረት ሊድን ችሏል፡፡ ከኢትዮጵያ ውጭም ፓርቲው ከነበረበት የተወሳሰበ ችግር ተላቆ በሁለት እግሩ ቆሞ እንዲሄድ ለማድረግ ፕሬዚዳንቱ በባህር ማዶ ያለውን ትግል መስመር ለማስያዝ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ በአገር ውስጥም የፕሬዚዳንቱ ተወካይ እና ከፍተኛ የአመራር አካላቱ ባለፉት አስር ወራት አያሌ ሥራዎችን አከናውነዋል፡፡ አጠቃላይ ክንውኑን በተመለከተም ከዚህ የሚከተሉት የፓርቲው አካላት ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡ እነሱም፡-

- የፓርቲው ፕሬዚዳንት ሪፖርት
- የኦዲት ሪፖርት
- ከየዞኑ የመጡ የፓርቲው ተወካዮች ሪፖርት
- የፓርቲው የወጣት ተወካይ ሪፖርት
- የፓርቲው የሴቶች ተወካይ ሪፖርት ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱት የየበኩላቸውን ለጉባኤው ሪፖርት ካቀረቡ በኋላ ጠቅላላ ጉባኤው በፓርቲው የወደፊት ተግባር ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችለው ውይይት የሚያካሂድበት አጀንዳ የተቀረፀ ስለሆነ ጉባኤው ወደ ዋና ተግባሩ እንዲገባ እጋብዛለሁ፡፡

አመሰግናለሁ